በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 4

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## ሚያዝያ ፳ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.

# የቀድሞ የሕይወት ታሪካችንና ጋብቻ

- የዛሬው ትምህርት የቀደመ መጥፎ ታሪክና ስለጋብቻ ሲሉ መጥፎውንም ገጽታ የማጽዳትን አስፈላፊነት የሚያመላክት ነው።
- ያን መጥፎ አጋጣሚ በጊዜ፣ በቦታ ወስነን ማስታወስ እንችላለን? ያ ታሪክ ሲፈጸም እግዚአብሔር በሕይወታችን በየት ነበር? እርሱ ቢኖር መጥፎው ታሪክ እንዴት ሊለወጥ ይችል ነበር?
- ያ መጥፎ ታሪክ ሲከሰት የነበሩትን ወይም ለጉዳቱ መንሥኤ የሆኑትን እናስታውሳቸዋለን? ይቅርስ እንላቸዋለን? ይቅር የማይሉ ሰዎች እንቅልፍ የላቸውም።
- ልጃችንን በመኪና የገደለውን ሰው በቀላሉ የማንረሳው ቢሆንም ይቅር ማለት ግን ይገባናል።
- የቀድሞ ሕይወታችን በዛሬው ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል። ይህንም አስመልክቶ አሥር ነጥቦችን እንመለከታለን።
  1. ባለፈ ሕይወታችን የደረሰብን ጉዳት ወይም አደጋ ምን ነበር? ማቆምስ እችል ነበር ወይ?
  2. ባለፈ ሕይወታችን ያሳለፍነው ንዴት ምን ነበር?
  3. የቀደሙ ቤተ ሰቦቻችን እነማን ነበሩ?
  4. ትምህርት የተማርንበት ወይም ከፍተኛ ትምህርት የተከታተልንበት ተቋም የቱ ነበር?
  5. በጾታዊ ጉዳይ ያለፈ ታሪካችን ምን ይመስል ነበር?
  6. የሥራ ዘርፋችን ወይም መደባችንና ሥራውን ለመሥራት የሚያስችለን መያዊ ብቃት ምን ነበር?
  7. ከዚህ በፊት ከጓደኞቻችን ጋር የነበረው ግኑኝነት ምን ይመስል ነበር?
  8. የገንዘብ አቅማችንና የገቢ ምንጫችን ምን ይመስል ነበር?
  9. አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነታችን ምን ይመስል ነበር?
  10. መንፈሳዊ ሕይወታችንስ ምን ይመስል ነበር?

## 1. ባለፉ ሕይወታችን የደረሰብን ጉዳት ወይም አደጋ ምን ነበር?

- የቃልም ሆነ አካላዊ ጉዳት ደርሶብን ተጎድተን እናውቃለን?
- በሌሎች ላይ የቃልም ሆነ የአካል ጉዳት አድርሰን እናውቃለን?
- ከዚህ በፊት የጎዱንን ሰዎች ፊት ለፊት ልንገናኛቸው የምንችልበት ጥንካሬ አለን?
- የጉዳቱ ጠባሳ ቢኖርም በመንገድ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ ወዘተ ልንገናኝ እንችላለን።
- እስካሁን ድረስ ከጉዳቱ ጋር በተያያዘ የምናስታውሳቸው ስሞች አሉን?
- ስማችንን ጠርተው የሚሰድቡን፣ ጫማ ወዘተ የሚወረውሩብን ገጥመውን ያውቃሉ?
- አንዳንዶች የመደፈር ወይም ክርስቲያናዊ ባልሆነ መንገድ ለዝሙት የመጋበዝ ትንኮሳ የገጠማቸው ይሆናሉ።
- ይህም ሁለት ሦስት ጊዜ በተደጋጋሚ ገጥሞን ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የገጠመን የት፣ መቼ፣ እንዴት ነው? ያን ጉዳት ማከም ችለናል? እንዴት ታከምነው?
- የሴቶች ግርዛት ራሱ በደል ወይም ጉዳት ማድረስ አድርጎ ይቆጠራል። በመጽሐፍ ቅዱስም አልተፈቀደም። በግርዛቱ ጊዜ የተፈጠረው የደም መፍሰስም ብዙዎችን ጎድቷል።
- ፍቅር ፈልገን ስንቀርብ ለበጎ የፍቅር ጥያቄያችን መልካም ምላሽ የሚሰጠን አጥተናል? እርዳታ፣ ርኅራኄን ፈልገን የሚመልስልን አጥተን እናውቃለን? እስካሁን ካስታወስነው ጎጂ ነው።
- ጉዳቶቹንስ ስናስባቸው ሕመሙ አሁንም ድረስ ይሰማናል?
- ዛሬም ቢሆን የተለያዩ ጥቃቶች በየቤቱ የሚከሰቱ አሳዛኝ ታሪኮች ናቸው።

# 2. ባለፈ ሕይወታችን ያሳለፍነው ንዴት ምን ነበር?

- በራሳችን፣ በሌሎች እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ የነበረን ንዴት ምንድር ነበር?
- **በራሳችን፡-** የኛ ኃላፊነት ባልነበረበት ጉዳዮች ንዴታችን ምንድር ነበር? አንድን ነገር ስናስታውሰን ያናድደናል? ራሳችን የሠራናቸውን ስህተቶች ስናስታውሳቸው በራሳችን ተናደን እናውቃለን?
- **በሌሎች፡-** መግለጽ ወይም ማስረዳት የምንችልበት አጋጣሚ በማጣት ወይም ባለመቻላችን፣ በተከሰተውም ሁኔታ በጣም በመናደዳችን፣ ወዘተ የተናደድንባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ? ይህ ራስን ወደማጥፋት ሊያመራ ይችላል፡፡
- እነዚህን ሰዎች ዛሬም ድረስ በሕይወት ካሉ ጤናማ በሆነ መንገድ ልንግባባቸው እንችላለን?፣ ለነዚህ ጉዳት ላደረሱብን ሰዎች ደብዳቤ ጽፈን ምን ያህል እንደጎዱን ገልጸንላቸው እናውቃለን?
- **በእግዚአብሔር፡-** የሕይወት ጓደኛዬ እንዲሞት/እንድትሞት ለምን ፈቀደ? ራሱን/ራሷን አጥፍታ ሊሆን ይችላል? ታዲያ እጊዚአብሔር ይህን ለምን ዝም አለ? ታዲያ ርኅራኄው የበዛ እግዚአብሔር ይህ ነው?
- ካንሰር እንዲኖርብኝ ስለምን ፈቀደ? አደረገ?
- ስንት ዘመን ሙሉ በጸሎት እየጠየቅሁህ እንደዚህ ዓይነት መከራ የማይበትን/የማይባትን ሰው/ሴት እንዳገባ ስለምን አደረግኸኝ?
- ሚስትህ ስለሞተች በእግዚአብሔር ተናደሃል?
- ባልሽ ስለሞተ በእግዚአብሔር ተናደሻል?
- ልጆች ስለሞቱባችሁ ወይም ስለታመሙባችሁ በእግዚአብሔር ተናዳችኋል? ችግሩ አሁን ተፈቷል?

# 3. የቀደሙ ቤተ ሰቦቻችን እነማን ነበሩ?

- ወላጆቻችን የሚከባበሩ ሆነን የመመልከት ዕድል ነበረን?
- ወላጆች፡- በአባትና እናታችን መካከል የነበረው የትዳር ሕይወት ምን ይመስል ነበር?
- አባት ሁልጊዜ አዛዥነት የሚያዘወትሩ ነበሩ? ጠጪስ ነበሩ?
- በወላጆቻችን መካከል የነበረው ግኑኙነት ልናስታውሰው የማንፈልገው መጥፎ ነበር?
- ከቤተሰቦቻችን የተነሳ ደኅንነት ወይም ዋስትና እንክብካቤ የማጣት ወይም ስሜት ይሰማን ነበር?
- ወላጆቻችን መልካም አርአያዎቻችን ነበሩ? በነገሮች የሚያበረታቱን ነበሩ ወይስ ዘወትር የሚወቅሱንና የሚጎዱን?
- ወላጆቻችን በእኛ ላይ ትዕግሥተኞችና የሚችሉን ነበሩ?
- ወላጆቻችን በቂ እንክብካቤ፣ ፍቅርና ርኅራኄ ያሳዩን ነበር?
- እናታችን አቅፋን የሳመችበት፣ አባታችን በጉልበቱ ላይ ያስቀመጠበት… ጊዜ ይታወሰናል?
- ጓደኞቻችን ወደ ቤታችን እንዲመጡ ይፈቅዱ ነበር፣ ሲመጡስ ያከብሯቸው ነበር?
- በቤተ ሰቦቻችን ወይም ጓደኞቻችን ፊት በሚጎዳን መልኩ ይቀጡን ነበር?
- ከወላጆቻችን ጋር ያለን ግኑኙነት መነጋገር ላይ የተመሠረተ ነው? ወይስ በመስማት ላይ ብቻ?
- ባንወዳቸውም አሁን ያለን ማንነት እንደ አባታችን ወይም እናታችን ያለ ነው? ለምን፣ ጠባያቸውን የማንወደው ከሆንን ለምን መልሰን እንደነርሱ እንሆናለን?
- ስለዚህ ይህን የትናንት መጥፎ ገጽታ እንዴት እንደምናሻሽለው እገዛን እንፈልግ፡፡
- ከቤተሰቦቻችን ጋር ያለን ግኑኙነት እውነተኛ፣ ሁሉንም መውደድ ያለበት ነው ወይስ ባለጠጎቹን ለይተን…. የምንወድበት ሌላውን የምንጠላበት ነው?

## 4. ትምህርት የተማርንበት ወይም ከፍተኛ ትምህርት የተከታተልንበት ተቋም የቱ ነበር?

- ትምህርት ቤቱ ምን ተብሎ ይጠራ ነበር? ማጥናት የምንፈልገው የትኛው ዩኒቨርስቲ ገብተን ነው?
- በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለን ሲደበድቡን የነበሩ መምህራንን እስካሁን እናስታውሳቸዋለን?
- በትምህርት ቤት እያለን ጥቃት ያደረሱብን መምህራን ቢኖሩስ ይታወሱናል?
- መጥፎ የትምህርት ቤታችን ስሞች አሁንም አይለየንም፣ ውጤታችን፣ መጥፎ ውጤት ስናገኝ ይደርስብን የነበረው መገለል፣ ወዘተ አሁንም አብሮን እየጎዳን አለ?

## 5. በጾታዊ ጉዳይ ያለፈ ታሪካችን ምን ይመስል ነበር?

- ከጾታ አጋሮቻችን ጋር ጤናማ ግኑኝነት እንዲኖረን ሆነን አድገናል?
- ከማግባታችን በፊት በሰንበት ት/ቤት እያለን ከተቃራኒ ጾታ ጋር ጤናማ ያልሆነ ግኑኝነት ነበረን?
- በጾታ የሚመስሉን መጥፎ የመረጃ ምንጮችን ሰጥተውን እምቢ ሳንል ቀርተን ተቀብለናል?
- ልቅ የወሲብ ፊልሞችን በመመልከት የተፈጠረብን ተጽእኖ አለ? ሳናደርግስ ስላለፈን እንቆጫለን?
- ራሳችንን በተመለከተ በጣም ቶሎ ስሜት ውስጥ የምንገባ ወይም የምንዘፈቅ ነበርን?

## 6. የሥራ ዘርፋችን ወይም መደባችንና ሥራውን ለመሥራት የሚያስችለን መያዊ ብቃት ምን ነበር?

- በምንሠራው ሥራ ወይም በአከናወንነው ነገር ውጤታማና የተሳካልን ነበርን?
- በዚህም የተነሳ ስለወደፊቱ ያለን ተስፋ የለመለመ ነው?
- በተሰማራንበት የሥራ መስክና ባለን ሙያ መመጣጠንና መረጋጋት አለን?
- ሥራችንን መቀየር እንፈልጋለን ወይስ ተመችቶናል? በሄድንበት ለቃል ጥያቄ ወይም ለኢንተርቪው ማለፍ አቅቶን የምንቸገር ነበርን ወይስ ሁልጊዜ የምንመረጥ?
- በሥራችን ጉዳይ አለቆቻችን ያለ አግባብ ይወስኑብናል ወይስ ስለ ሥራችንና ስለ ብቃታችን አድንቀው ያመሰግኑናል?

## 7. ከዚህ በፊት ከጓደኞቻችን ጋር የነበረው ግኑኝነት ምን ይመስል ነበር?

- ጓደኞች ነበሩን፣ ምን ዓይነት፣ መትፎ ሱስ አለን…? ለእድገታችን ምክንያት ናቸው ወይም ለመበላሸታችን?
- ከቤት ውጪ ስንሆን ለመዝናናት ስንወጣ የምናደርገው ምንድር ነው?
- በሱሰኝነት የተያዝንበት መጥፎ ሁኔታ አለ?
- መልካም ባልሆኑ የስሜት ፍቅር ድርጊቶች የምንታወስ ነን? ቃል ኪዳን አፍርሰን እናውቃለን፣ ከዚህም ከዚያችም ጋር ግልጽ በሆነ መንገድ በመውደቅ መታወቂያ ምልክት የተሰጠን ነን?

## 8. የገንዘብ አቅማችንና የገቢ ምንጫችን ምን ይመስል ነበር?

- እስካሁን ድረስ የምንከፍለው ብድር ወይም ዕዳ አለብን?
- ጥቂትም ቢሆን የምንቆጥብበት የቁጠባ የሂሳብ ደብተር አለን?
- ገንዘባችንን ወይም ገቢያችንን ያለአግባብ እንጠቀማለን? ወሩ ሳይደርስ ደመወዛችንን በመብላትና በመጠጣት የምንጨርስ ነን?

## 9. አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነታችን ምን ይመስል ነበር?

- መላ አካላችንና አእምሮአችን ጤናማና በአግባብ ማከናወን የሚችል ነው?
- መጠጥም ሆነ ሌላ ተፈጥሮአዊ ያልሆነ ምክንያት ትክክለኛ እንቅስቃሴውያችንን የገደበው አይደለምን? ከጋብቻ በፊት ብንመረመረው መልካም ነው ብለን እናምናለን?

## 10. መንፈሳዊ ሕይወታችንስ ምን ይመስል ነበር?

- በእውነተኛይቱ ቤተ ክርስጢያን ያደግን ነን? ሃይማኖታችንን ትተን የሄድንበት ወይም ሃይማኖታችንን የለወጥንበት ጊዜ ነበር?
- ለጸሎት፣ ቅዳሴ ለማስቀደስ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብ፣ ለመማር፣ ወዘተ የተመደበ የታወቀ መርሐ ግብር አለን?
- የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ይሰማናል? የንስሐ አባት አለን? የንስሐ አባታችን የሚሰጡንን ምክር እንከታተላለን? ማንኛውንም ጉዳይ በግልጽ ለነፍስ አባታችን ገልጸን እንነጋገራለን?

- እነዚህ ሁሉ ያልታረሙ የቀድሞ ታሪኮችን ጉዳዮች በአእምሮአችን እያሉ ወደ ትዳር ለመግባት አንድፈር፡፡
- ከገባንም ያልታረመውን የሕይወታችንን ችግር ከንስሐ አባታችን ጋር ተነጋግረን እናስተካክለው፡፡
- በሁሉ የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን፡፡

# ምንባብ

- “ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፦ አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ በወንበዴዎችም እጅ ወደቀ፤ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም በሕይወትና በሞት መካከልም ትተውት ሄዱ።
10 31 ድንገትም አንድ ካህን በዚያ መንገድ ወረደ አይቶትም ገለል ብሎ አለፈ።
10 32 እንዲሁም ደግሞ አንድ ሌዋዊ ወደዚያ ስፍራ መጣና አይቶት ገለል ብሎ አለፈ።
10 33 አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ አይቶትም አዘነለት፥
10 34 ቀርቦም ዘይትና የወይን ጠጅ በቍስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው፥ በራሱ አህያም ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማደርያ ወሰደው ጠበቀውም።
10 35 በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና። ጠብቀው፥ ከዚህም በላይ የምትከስረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ አለው።
10 36 እንግዲህ ከነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል?
10 37 እርሱም፦ ምሕረት ያደረገለት አለ። ኢየሱስም፦ ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ አለው። ***<u>ሉቃ 10፡32-37።</u>***

- “ተንበርክኮም። ጌታ ሆይ፥ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ።” ***<u>የሐ. ሥራ 7፡60።</u>***

- “ኢየሱስም፦ አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ።” ***<u>ሉቃ 23፡34።</u>***

E-mail:
kesisolomon3@gmail.com

Web Site:
www.zeorthodox.org

... ክፍል አምስት ይቀጥላል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።